በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS

ፕሬስ መግለጫ PRESSRELASE

# ሁለተኛው የኢትዮ- ናይጄሪያ የሚኒስትሮች የጋራ ኮሚሽን ስብሰባ በአቡጃ ተጀመረ



በሁለተኛው የኢትዮ- ናይጄሪያ የሚኒስትሮች የጋራ ኮሚሽን ስብሰባ ላይ ለመሳተፍ በኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁ የተመራ የልዑካን ቡድን ወደ አቡጃ ይገኛል፡፡

ውይይቱ የሁለቱ አገሮች ኢኮኖሚያዊና ፓለቲካዊ ግንኙነቶች በሚጠናከሩባቸው ጉዳዮች ላይ ያተኩራል፡፡ በዚህም የተለያዩ ስምምነቶች የሚፈረሙ ሲሆን የሁለቱን አገራት ወዳጅነት የሚያሳድጉ ጠቃሚ ምክክሮች ይደረጋሉ ተብሎም ይጠበቃል።

ክቡር ሚኒስትሩ ከእውቁ ናይጀሪያዊ ባለሃብትና ዓለም አቀፍ ኢንቨስተር አሊኮ ዳንጎቴን በናይጀሪያ አቡጃ አነጋግረዋል።

በኢትዮጵያ እያካሄዱ ላለው ኢንቨስትመንት ምስጋናቸውን በማቅረብ፣ መንግስት ባለሀብቱ በኢትዮጵያ ለሚያደርጉት የልማት እንቅስቃሴ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልጸውላቸዋል፡፡

ኢትዮጵያና ናይጄሪያ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከጀመሩበት እ.ኤ.አ. ከ1960 ዎቹ ጀምሮ ሁለቱ አገሮች ኤምባሲያቸውን በመክፈት የሁለትዮሽ ግንኙነታቸው እንዲጎለብት በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

በሁለቱ አገሮች መካከል የተፈረሙ ስምምነቶች

- የአየር አገልግሎት ስምምነት፣
- የንግድ ስምምነት፣
- የባህል፣ ሳይንስና የትምህርት ትብብር፣
- በባህልና በቱሪዝም መስክ፣
- በግብርናው መስክ፣

በዲፕሎማቲክ መስክ ስልጠና ለመስጠት፣ ዋነኞቹ ሲሆኑ በተለያዩ መስኮች የጋራ መግባቢያ ሰነዶች ተፈርመዋል፡፡

E-mail spokesperson@mfa.gov.et facebook @mfaEthspokesperson, Twitter @mfaEthspokesperson,
YouTube https://www.youtube.com/channel/UCa_KUDpwCLMWyyQIjfilgZg ☎ 011-5-15 8928/011-5-53 6731 Fax 011-5-51-43-00 ✉393
Addis Ababa,Ethiopia

የመጀመሪያው የኢትዮ-ናይጀሪያ የሚኒስትሮች የጋራ ኮሚሽን ስብሰባ እ.ኤ.አ. በ2006 በአዲስ አበባ መካሄዱ ይታወሳል፡፡

**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**

**ቃል አቀባይ ጽ/ቤት**

**ህዳር 25 ቀን 2010 ዓ.ም.**

E-mail spokesperson@mfa.gov.et facebook @mfaEthspokesperson, Twitter @mfaEthspokesperson,
YouTube https://www.youtube.com/channel/UCa_KUDpwCLMWyyQIjfilgZg ☎ 011-5-15 8928/011-5-53 6731 Fax 011-5-51-43-00 ✉393
Addis Ababa,Ethiopia